## ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04032 በመጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40698 በኅዳር 7 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሁከት ተፈጥሮበታል የሚሉት ቤት አመልካች ለብድሩ አከፋፈል በዋስትና በያዘው በካርታ ቁጥር 045/91 ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ ይህንን ቤት ጨምሮ ለመሸጥ ስለሚችል ሁከት አልተፈጠረም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁጥር 29005

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1. ግርማቸው ይላላ ቀረቡ፡፡

2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ይሰጠኝ በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተው በ2ኛው ተጠሪ ላይ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በሁለቱ መካከል የተሰማውን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ 2ኛ ተጠሪ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ ይስጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክሩ የእኔን መብት የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን የተመለከተ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ተቃዋሚው /የአሁኑ አመልካች/ ተጠሪነቱ ለ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ አልነበረም የሚባል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን

ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ፣ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በአቃቂ ክፍለ ከተማ ስር የተደራጀ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 10/2/ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሉት ክፍለ ከተሞች የየራሳቸው ምክር ቤት፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ ኖሯቸው የተደራጁ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 30 እንደተደነገገውም ክፍለ ከተሞች ባልተማከለ የስልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት ይሰራሉ፤ በሥራቸው የሚገኙትን ቀበሌዎችም ያስተዳድራሉ፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ አንቀጽ 10 በተመለከተው አይነት የከተማው አስተዳደር የስልጣን አካላት የተደራጁ ሲሆን፣ ከነዚህ አንዱ ክፍለ ከተማ ነው፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው እና በሕግ በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ በራሱ ኃላፊነት የሚንቀሳቀስ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በሁለተኛ ተጠሪነት የተመዘገበው አካል ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ ክፍለ ከተሞች ካርታ እና የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ስልጣንና ተግባር በቻርተሩ እና ቻርተሩን መሠረት በማድረግ በወጡት የከተማው አስተዳደር አዋጆች እንደተሰጣቸው አረጋግጦአል፡፡ በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካወጣቸው አዋጆች አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎችና የቀበሌዎች አስተዳደር" ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁ. 1/95ን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 18/97 ሲሆን፣ ይህ አዋጅ በክፍለ ከተማው ውስጥ ያለውን ቦታ የማስተዳደር ስልጣን የክፍለ ከተማው እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቦታ ማስተዳደር ደግሞ ለአሁኑ ክርክር መነሻ



የሆነውንም እንደሚያጠቃልል በአዋጁ አንቀጽ 2 ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መነሻነት ውሣኔ የተሰጠበት ጉዳይ እኔን የሚመለከት ነው በማለት መቃወሚያ ያቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይም በሱ የስልጣን ክልል ውስጥ የሚከናወን ነው፡፡ በመሆኑም አያገባህም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48511 ሚያዝያ 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47682 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩ እሱን በቀጥታ የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበውን መቃወሚያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተቀብሎ ክርክሩን በመስማት ይወስን ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ